# የሀገራችንን አንድነትና የሕዝባችንን ሰላምና ደህንነትን ማረጋገጥ ከሁሉም ጉዳይ ቅድሚያ ሊሰጠው ይገባል፡፡

(ከኢትዮጵያ ሶሻል ዴሞክራቲክ ፓርቲ የተሰጠ መግለጫ)

የኢህአዴግ አገዛዝ በተለያዩ ሀገሮች ሰላም የማስከበር ሥራ እየሠራሁ ያለሁት የዓለም የሰላም አስከባሪ ኃይል ነኝ እያለ ብዙ ቢያወራም ባለፉት 26 የአገዛዙ ዓመታት ሕዝባችንን ከፋፍሎ የሚገዛበት ስልቱን እየቀየሰና እየተገበረ ብሔሮችና ብሔረሰቦች እንደዚሁም አጎራባች ክልሎች እርስበርስ የሚጋጩበትን ሁኔታ ፈጥሮ በመቆየቱ የሀገራችንን አንድነትና የሕዝባችንን ሰላምና ደህንነትን እጅግ አሳሳቢ ሁኔታ ላይ ጥሎት ይገኛል፡፡ ግዛታቸውን የማስፋፋት አባዜ የተጠናወታቸው የአገዛዙ የክልል ባለሥልጣናቶችና ካድሬዎቹ በክልሎችና ብሔር ብሔረሰቦች መካካል የሚፈጥሩት ግጭት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ በአሁኑ ወቅት በብዙ አከባቢዎች የበርካታ ሰላማዊ ዜጎቻችንን ሕይወት በመቅጠፍና ንብረት በማውደም ላይ ይገኛል፡፡ በዚህም ክስተት የእራሱዋ እያረረባት የሰውን ታማስላለች እንዲሉ በብዙ ሀገሮች ሰላም እያስከበርኩ ነኝ የሚለው የኢህአዴግ አገዛዝ በሀገራችን ውስጥ የሕዝባችንን ሰላምና ደህንነት የማስከበር መንግሥታዊ ኃላፊነቱን በአግባቡ ለመወጣት እንኳን እንዳልቻለ ከጊዜ ወደ ጊዜ የበለጠ ግልጽ እየሆነ ይገኛል፡፡

በአሁኑ ወቅት በክልሎች ድምበር ሰበብ በኦሮሚያና በሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥታት አዋሳኝ አከባቢዎች ተቀስቅሶ ለወራት ጊዜ በተከታታይ እየተካሄደ ያለውና የብዙ ዜጎችን ሕይወት በመቅጠፍ ላይ ያለው ጦርነት፣ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል በሰገን አከባቢ ሕዝቦች ዞን በሚገኙት የአማሮና የቡርጂ ወረዳዎች በሚኖሩት የኮሬና የቡርጂ ብሔረሰቦች ላይ የተከፈተውና እየተካሄደ ያለው የግዛት ማስፋፋት ጦርነትና በኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ ሐረርጌ ዞን በሚገኘው የአወዳይ ከተማ በሚኖሩ በኢትዮጵያ ሶማሌ ብሔር ተወላጆች ላይ የተፈጸመው ጅምላ ግዲያና በሶማሌ ብሔራዊ ክልል ነዋሪ በነበሩ የኦሮሞ ብሔር ተወላጆች ላይ እንደዚሁም በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልል በባሌ ዞን በአንጌቶና በሌንሳሞ ወረዳዎች ነዋሪ በነበሩ የሲዳማ ብሔር ተወላጆች ላይ የተከፈተው ጦርነት የኢህአዴግ አገዛዝ ሀገራችንን በአሁኑ ወቅት ያደረሰበትን አሳሳቢና አስጊ ሁኔታ አመላካቾች ናቸው፡፡ በዚሁም መሠረት በኦሮሚያና በሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥታት አዋሳኝ አከባቢዎች ተቀስቅሶ እስከ አሁን መፍትሔ ሳይሰጠው ለወራት በቆየው ግጭት ከሁለቱም በኩል ከ400 በላይ ዜጎቻችን ሕይወት የጠፋ ሲሆን ከ1000000 በላይ ዜጎቻችንም ከቤት ንብረታቸው ለመፈናቀል ተገደዋል፡፡

ከዚህም ሌላ በዚሁ የድንበር ማስፋፋት እንቅስቃሴ በቅርቡ ማለትም ከመስከረም 1 ቀን 2010 ጀምሮ በአማሮ ወረዳ ነዋሪ በሆነው የኮሬ ብሔረሰብና በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልል በገላና አባያና በቡሌ ሆራ ወረዳ ነዋሪ በሆኑት የጉጂ ኦሮሞ ሕዝብ አዋሳኝ ድንበሮች አከባቢዎች አዲስ ግጭት የተቀሰቀሰ ሲሆን ከመስከረም 3 ጀምሮ ደግሞ በቡርጂ ወረዳ ነዋሪ በሆኑት የቡርጂ ብሔረሰብ አባላትና በኦሮሚያ ክልል ቡሌ ሆራ ወረዳ ነዋሪ በሆኑት የጉጂ ኦሮሞ ሕዝብ አዋሳኝ ድንበሮች አከባቢዎች አዲስ ግጭት ተቀሰቅሶአል፡፡ በዚህ ግጭት በኮሬ በኩል የ7 ዜጎቻችን ሕይወት ሲጠፋ፣ 14 ዜጎቻችን ቆስለዋል፡፡ በሺህዎች የሚቆጠር የ12 ቀበሌዎች ነዋሪ ሕዝብ የእህል ክምርም ተቃጥሎአል፡፡ በተለይም ጀሎ ተብሎ የሚጠራ ቀበሌ ነዋሪዎች መኖሪያ ቤትና ንብረት ሙሉ በሙሉ ሊባል በሚችል ደረጃ ተቃጥሎና ተዘርፎ ሊወድም ችሎአል፡፡አንድ የኦርቶዶክስ እና አንድ የቃለሕይወት ቤተክርስቲያናት ንብረቶችም ተዘርፈዋል፡፡

ከቡርጂ በኩል ደግሞ የ3 ሰው ሕይወት ሲጠፋ በ7 ሰው ላይ የመቁሰል አደጋ ደርሶአል፡፡ በመቶዎች የሚቆጠሩ የጤፍና የበቆሎ ክምሮችም ተቃጥለዋል፡፡ በጉጂ ኦሮሞ በኩልም 8 ዜጎቻችን እንደሞቱና በርካቶች እንደቆሰሉ ለማወቅ ተችሎአል፡፡ ቀደም ሲልም የኮሬ ብሔረሰብና በኦሮሚያ ክልል በገላና አባያና በቡሌ ሆራ ወረዳ ነዋሪ በሆኑት የጉጂ ኦሮሞ ሕዝብ መካከል ከሐምሌ 16 ቀን 2009 ጀምሮ እስከ ሐምሌ 22 2009 ዓ ም ድረስ በዚሁ የድንበር ጉዳይ ምክንያት በተነሳው ግጭት የበርካታ ዜጎቻችንን ሕይወት እንደጠፋና ከፍተኛ ግምት ያለው ንብረትም እንዳወደመ ይታወሳል፡፡ (ይህንን ጉዳይ በሚመለከት ፓርቲያችን ሐምሌ 25 ቀን 2009 ዓ ም መግለጫ ማውጣቱም ይታወሳል፡፡)
ይባስ ብሎም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ብቻ ከድንበር አከባቢ ግጭቶች ርቀው በሚኖሩ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በምሥራቅ ሀረርጌ ዞን ባለው የአወዳይ ከተማ ነዋሪ በነበሩ የሶማሌ ብሔር አባላት በሆኑ ዜጎቻችን ላይ በተወሰደው አሰቃቂ የጅምላ የጊዲያ እርምጃ ከ50 በላይ የኢትዮጵያ የሶማሌ ብሔር አባላት ተገድለዋል፡፡ ከሶማሊያ ብሔራዊ ክልል ከተሞች ደግሞ ከ50000 በላይ የኦሮሞ ብሔር ተወላጆች እንደፈናቀሉ ተደርገዋል፡፡ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልል በባሌ ዞን ነዋሪ በነበሩት የሲዳማ ብሔረሰብ አባላት ላይ በተከፈተው ከመኖሪያ አከባቢያቸው የማባረር ጥቃት 6 ሰዎች ሞተው በርካቶች ቆስለዋል፡፡
ከ1700 በላይ አባወራዎችና ከ5000 በላይ የቤተሰብ አባላት ያሉበት የሲዳማ ብሔረሰብ አባላት ከቤት ንበረታቸው ለመፈናቀል ተገደዋል፡፡ እንደዚሁም በኦሮሚያ ክልል በቡሌ ሆራ ከተማ ነዋሪ በሆኑ የቡርጂ፣ የኮሬና የሲዳማ ብሔረሰብ አባላት ላይ በተፈጸመው ጥቃት 3 የኮሬ፣ 2 የቡርጂ እና 1 የሲዳማ ብሔረሰብ አባላት የተገደሉ ሲሆን 7 ዜጎች ደግሞ ቆስለዋል፡፡ እንደዚሁም በርካታ የመኖሪያ ቤቶቻቸውና የእህል ክምሮችም ተቃጥሎአል፡፡ በሺህዎች የሚቆጠሮ የቤት እንሰሳቶችና በብዙ ሚሊዮን ብር የሚገመትና በእርሻ ላይ የነበሩና ያልተሰበሰቡ የእርሻ ምርቶቻቸውም ተዘርፎባቸዋል፡፡

በአሁኑ ወቅት እየተካሄዱ ባሉት በእነዚሁ እጅግ አሳአሳቢ በሆኑ ግጭቶች ከሁሉም በላይ ችግሩን የከፋ መልክ እያስያዘ ያለውና ለሀገራችን አንድነትና ለሕዝባችን ሰላምና ደህንነት አስጊ እየሆነ ያለው ነገር ደግሞ በግጭቶቹ የክልላዊ መንግሥታት የጸጥታ ኃይሎች ወገን ለይተው እየተሳተፉ ጥቃት እያደረሱ መሆኑ ነው፡፡ ይህም በአገዛዙ አመራር አካላት ጭምር በይፋ እየተገለጸ የሚገኝ ጉዳይ ስለሆነ አስቸኳይና የማያዳግም የእርምት እርምጃ ካልተወሰደ ለሀገራችን አንድነትና ለሕዝባችን ሰላምና ደህንነት የከፋ አደጋ ሊያስከትል እንደሚችል ኢሶዴፓ ይገነዘባል፡፡
ስለዚህም የሚከተሉት እርምጃዎች በሚመለከታቸው አካላት በአስቸኳይ እንዲወሰዱ አበክሮ ይጠይቃል፡፡
1ኛ፡- በግጭቶቹ የኢህአዴግ አገዛዝ የአከባቢ ባለሥልጣናት፣ ካድሬዎችና የጸጥታ ኃይሎች ወገን ለይተው ሰላማዊ ሕዝብን እያጠቁና እያስጠቁ እንደሆነ ከራሳቸው ከመንግሥት ባለሥልጣናት ሳይቀር በይፋ እየተገለጸ ቢሆንም እስከ አሁን በተጨባጭ ተጠያቂ የሆነ አካል አለመኖሩ ችግሩን እያባባሰው ይገኛል፡፡ ስለዚህም ግጭቶቹን የቀሰቀሱትና የመሩት የመንግሥት ባለሥልጣናትና አካላት ሁሉ ተገቢው ሕጋዊ እርምጃ ተወስዶባቸው ውጤቱ ለሕዝብ በይፋ እንዲገለጽ፣
2ኛ፡- የኢፌዴሪ ሕገመንግሥት አንቀጽ 32 ንዑስ 1 ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ወይም በሕጋዊ መንገድ ሀገሪቱ ውስጥ የሚገኝ የውጭ ዜጋ በመረጠው የሀገሪቱ አከባቢ የመዘዋወርና የመኖሪያ ቤት የመመሥረት፣ እንዲሁም በፈለገው ጊዜ ከሀገር የመውጣት ነፃነት አለው፡፡ ተብሎ የተደነገገውን በመተላለፍ ዜጎችን ክልሉ የሚጠራበት ብሔር አባል ባለመሆናቸው ብቻ ለብዙ ዓመታት ቤት ንብረት አፍርተው ከኖሩበት አከባቢ እንዲፈናቀል ማድረግ የሕገመንግስትና የሰብአዊ መብቶች ጥሰት ስለሆነ በእነዚሁ ግጭቶች የሞቱት፣ የቆሰሉት፣ የተፈናቀሉትና የተዘረፉት ዜጎች ሁሉ ለደረሰባቸው ጉዳት ተገቢው ካሳ በመንግስት ተከፍሎአቸው ተፈናቃዮቹ በየመኖሪያቸው ተመልሰው

እንዲቋቋሙ እንዲደረግ፣ ለወደ ፊቱም ተመሳሳይ ጥቃቶች በየክልሉ በሚኖሩ ዜጎች ላይ እንዳይፈጸም መንግሥት ሙሉ ኃላፊነት ወስዶ ተገቢውን ጥበቃ እንዲያደርግላቸውና በሀገራቸው በነጻነት የመኖር መብታቸውን እንዲያከብርና እንዲያስከብር፣

3ኛ፡- መላው የሀገራችን ሕዝቦችም ሀገራችን ለሁላችንም የጋራችን እንደሆነች በመገንዘብ በክልሎች ማስፋፋት ዓላማም ሆነ በሌሎች ሕዝባችንን በሚያጋጩ የጥፋት ዓላማዎች በመነሳሳት የገዥው ፓርቲ ባለሥልጣናትና ካድሬዎች እንደዚሁም ሌሎች ጠባብና ትምክህተኛ ዓላማ አንግበው የሚንቀሳቀሱ ኃይሎች በሚያካሂዱት እርበና ብስ ቅስቀሳ በመገፋፋት ለዘመናት የገነቡትን ማሕበራዊ ትስስራቸውን የሚያፈርስ ግጭት ውስጥ ከመግባት ተቆጥበው አንድነታቸውንና አብሮነታቸውን እንዲያጠናክሩ ኢሶዴፓ ጥሪውን ያስተላልፋል፡፡

ለሕዝባችን ሰላምና ደህንነትና ለሀገራችን አንድነት ቅድሚያ ሊሰጠው ይገባል፡፡

የኢትዮጵያ ሶሻል ዴሞክራቲክ ፓርቲ

መስከረም 10 ቀን 2010 ዓ ም

አዲስ አበባ